የ ድ ሬ ዳ ዋ   አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E  N E G A R I T  G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

| | | |
|---|---|---|
| አንደኛ ዓመት ቁጥር 7<br>ድሬዳዋ ጥቅምት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. | በትሬ[illegible] አስተዳደር<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 1st Year No. 7<br>DIRE DAWA – 1st November, 2008 |


## አዋጅ ቁጥር 7/2001

**የድሬዳዋ አስተዳደር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ግኝት ማስፈፀሚያ አዋጅ**

በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ እየተሰራባቸው ያሉ ሕጎችና የአሰራር ልምዶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተገኙ አዳዲስ አሰራሮችን ለመተግበር የማያስችሉ ሆነው በመገኘታቸው፤

በአስተዳደሩ ውስጥ ተጠያቂነትን የሚያስከትል፣ ግልጽነትን የተላበሰ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በብቃት በመስጠት ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO.7/2008

**A PROCLAMATION ENACTED FOR THE IMPLEMENTATION OF DIRE DAWA ADMINISTRATION BUSINESS PROCESS RE-ENGINEERING PROGRAM**

WHERE AS, its the laws and customary practices on being used by the offices found in the administration that are found not enabling for the implementation of the new findings of the Business process re-engineering program.

WHERE AS, its necessitated to create a conducive condition to implement the study of the Business Process Re-engineering in a

productive manner; in-order to, delivery an accountable, fast and expeditious service in our endeavor to get out of poverty.

መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ተግባራዊ ሲሆን የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሣቦችና የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በመታመኑ፤

በጥናቱ የተደረሰባቸውን የአሰራር ሥርዓቶችና የአደረጃጀት ማሻሻያዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሚል መነሻ በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎች ለመ ቀየር ቢታሰብ ጊዜ የሚወሰድ ከመሆኑ ባሻገር ጥናቱ በሙከራ ታይቶ ውጤታማነቱ ባልተረ ጋገጠበት ሁኔታ መቀየርም አዳጋች በመሆኑ፤

አስተዳደሩ እያስመዘገበ ያለውን አበረታች ኢኮኖ ሚያዊ እድገት ቀጣይነት በማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግን ባታ ሥር እንዲሰድ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር በማስፈለጉ፣

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416 /1996 አንቀጽ 12/2/ /ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል::

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ «የድሬዳዋ አስተዳደረ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ግኝት ማስፈ ፀሚያ አዋጀ ቁጥር 7/2001 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. «መሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ግኝት» ማለት በአስተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራን እንደገና በማደራጀት ፈጣ ንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲ ቻል ለበርካታ ወራት በተለያዩ የሥራ ሂደቶች የተካሄደውን ጥናት ውጤት የሚ ያመለክት ነው::

WHERE AS, its believed to make the implementation of the Business Process Re-engineering based on concept of democracy and supremacy of the law.

WHERE AS, its found difficult and time consuming to change the operating laws with a view to implement the working procedure and the reform of organizational structure forced by the study; for a pilot study whose fruitfulness is not yet ascertained.

WHERE AS, its necessitated to create a conducive environment to ascertain the sustainability for the encouraging economic development being registered by the administration by promoting good governa-nce and democratization.

NOW, THEREFORE, Dire Dawa Administrative Council in accordance with the power vested on it by article 12(2) (a) of Dire Dawa Administration Charter has proclaimed the following.

**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as "a proclamation enacted for the implement-tation of the finding of Dire Dawa Administration Business process re-engineering program proclamation No 7/2008''

**2. <u>Definition</u>**

In this Proclamation unless the context requires other wise;

1. ''Business Process Re-engineering study finding'' means a result of the study conducted in different work process for several months, to enable a

fast and expeditious delivery of service by re-organizing works in various offices of the administration.

2. «የመንግሥት መሥሪያ ቤት» ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋ ቋመና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከአስ ተዳደሩ በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የአስተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው::

3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ተግባራዊ በሚያደርጉ የመንግሥት መስ ሪያ ቤቶች ላይ ብቻ ይሆናል::

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል አስፈላጊነቱ በካቢኔው ከታመነ በትና ውሣኔ ከተሰጠበት በሥራ ሂደቱ ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ አዋጁ መሠራታዊ ሂደት ለውጥ ባልጀመሩ የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ላይም ተፈፃሚ ለሆን ይችላል::

4. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ለአስተዳደሩ ካቢኔ አቅርበው ማጸደቅ ይኖርባቸዋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተደነ ገገው መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፀደቀውን ለውጥ በሥራ ላይ ሲያ ውሉ ለወጡ በሥራ ላይ ካለ በአስተዳደሩ ከወጣ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ጋር ግጭት ቢፈጥር በጥናት የተገኘው አዲስ አሠራር ተፈፃሚ ነት እንዲኖረው ለማስቻል ሊሻሻል የሚገ ባውን ረቂቅ ሕግ በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 መሠረት ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያቀርባሉ::

2. "Government Office" means an office independently established by proclamation or directive and administered fully or partially by a budget allocated by government.

## 3. Scope of application

1. This proclamation is made applicable only to those government offices; which have been completed and implemented there BPR study.

2. Not with standing sub-article 1 of this provision to enable the applicability of this proclamation; where the cabinet of the administration believed its importance in matters that do have communality this proclamation may be made applicable on governmental offices which have not yet started to conduct the study of Business Process Re-engineering

## 4. Transitional provisions

1. Governmental offices found in the administration shall complete their Business Process Re-engineering study and present the same to the cabinet of the administration for approval.

2. Based on the provision of sub article (1) of this article, whenever they implement the approved study, if the change contradict with the working proclamation, regulation and directives of the administration or with customary practices, the draft law that need an amendment shall be presented to an organ that do have a power to

enact law in accordance with the Dire Dawa Administration Charter Proclamation No. 416/2004.

5. <u>አዋጁ በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ የሚውለው ለአስተዳደሩ ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት ብቻ ይሆናል።

6. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. በአስተዳደሩ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአሠራር ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው በምን መልኩ ወደ ሥራ መግባት እንዳለባቸው የሚደነግጉ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ይወጣሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት እና ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልገውን ደንብና መመሪያ የአስተዳደሩ ካቢኔ ሊያወጣ ይችላል።

7. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ድሬዳዋ ጥቅምት 22 ቀን 2001 ዓ.ም.

አደም ፋራህ

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ

5. **<u>Duration of the proclamation</u>**

This proclamation shall stay in effect only for two years after its presented and approved by the council

6. **<u>Power to issue regulations and directives</u>**

1. Government offices found in the administration may enact important directives and regulation that decide the way to fallow for the implement ation of Business Process Re-engi neering study.
2. Based on sub article (1) of this article the cabinet of the administration may enact regulation and directives for the full scale execution of this proclamation.

7. **<u>Effective date</u>**

This proclamation shall enter into force as of the 1st day of November, 2008.

**Done at Dire Dawa, this 1st day of November, 2008**

**Adem Farah**

**Mayer of Dire Dawa Administration**